# ምስለ መለስ፡ የማንነቱ ገፅታ

በህይወት በኖረባቸው ዘመናት ባቆራረጣቸው ምዕራፎች ስለነበረው ማንነትና ስለመልካም ምግባሩ፡ እንዲነገርለት ቅንጣትም ፍላጎት ያልነበረው መለስ ዜናዊ በዚህች አለም በቆየባቸው 57 አመታት በተለይም በወጣትነትና በጐልማሳነት ዘመኑ ባሳለፋቸው ምዕራፎች እንደምን የታላቅ ታሪክ ባለቤት መሆን እንደቻለ ዛሬ ለመናገር እንገደዳለን፡፡



የመለስ ሕይወትና ተግባር ከመጀመሪያው እስከመጨረሻው በትግሉና በድርጅቱ የታቀፈ ቢሆንም፣ በዚህ መራራ ዕለት በማንነቱ ገጽታ ላይ እናተኩራለን፡፡ ገፅታውን አካሉ ከሆነው ትግልና ከመራው ድርጅትና የመንግሥት ታሪክ ወጣ አድርገን ብናስተውለው መለስን ከጓዶቹም እንኳ ቢሆን እጅጉን ለየት የሚያደርጉት ባህርያቱ በጉልህ ይታያሉ፡፡ የመራው ትግል፣ ድርጅትና መንግሥት ዋና ዋና ድሎች፣ የሥራ ፍሬዎችና ቅርሶች - - ለምሳሌ፣ በታሪካችን ምንጊዜም ያልታየና ያላሰለሰ ኢኮኖሚያዊና ማኅበራዊ አኩሪ እድገት - - እንኳን በአገራችን በመላው ዓለም ዕውቅና አግኝቷል፡፡ ለትኩረታችን መነሾ ከሁሉም በላይ ሊታወቅ የሚገባው፣ መለስ ስለራሱ መናገርም ሆነ መስማት የማይወድ የነበረ ከመሆኑ አኳያ በአንደበቱ ለማለፍ ዕድል የተነሳች ዋናዋ ቃል "እኔ" ሳትሆን አትቀርም፡፡

ለመቅደም፣ ለመታወቅ፣ ለመወደድ እማይሻ ሰው በመሆኑ ሰሞኑን በመላ አገሪቱ ባስተጋባው የሃዘን እሮሮ እንደታየው እንዴት የተከበረና የተፈቀረ ገናና መሪ ለመሆን እንደበቃ ቢታወስ አርአያው አብነት ለሆነላቸው ሁሉ፤ በተለይም ለኢትዮጵያና ለመላው አፍሪቃ ወጣት ትውልድ፤ ማንን እንደሚከተሉ በግልጽ ያመላክት ይሆናል፡፡

መለስ ለወጣቶች "የእኔ ትውልድ ባለፈበት የጦርነትና የሰቆቃ ህይወት እንዳያልፉና የተሻለም ቀን እንዲመጣላቸው እመኛለሁ ይላል፡፡ ትግሉን የጀመረ አይጨርሰውም፣ የእኛ ትግል የዱላ ቅብብል እንጂ የማራቶን ሩጫ አይደለም፣ ስለዚህም ወጣቶች ተኪዎቻችን ናቸውና እናስተምራቸው፣ እናብቃቸው የሚል ፅኑ አቋምም አለው"፡፡ እናም የሀገራችን ወጣቶች እንደ አብነት ከሚያዩት ከዚህ ታላቅ ሰው መውረስ ያለባቸውን ባህርያት እንዲያውቁና ምን መከተል እንዳለባቸው እንዲገነዘቡ የማንነቱን ገፅታ ከአንኳር ተግባሩ ጋር አያይዘን ማሳየትን መረጥን፡፡

በመልካም ተግባራቸውና በሰብዕናቸው ደምቀውና አንፀባርቀው ከመቃብር በላይ ስማቸው ጐልቶ ከሚሰማው ታላላቅ ሰዎችና አለማችን ለቅፅበት አይታቸው ካለፉ ተወርዋሪ ኰከቦች አንዱ የሆነውን የመለስ ዜናዊን ማንነትና በታሪክም ውስጥ ያለውን አኩሪ ቦታና ዋነኛ ጉዳዮች በአጭሩና በቅንጭቡ መላ ወዳጆቹና አጋሮች ይሰሙትም ዘንድ ምስለ መለስን እነሆ!

## መለስ ባለራዕዩ፣ የለውጥ ጠንሳሽና መሪ!

መለስ በ1971 ኢ.ም. በተካሄደው የህወሓት 1ኛ ድርጅታዊ ጉባኤ የማዕከላዊ ኮሚቴ አባል ሆኖ ከተመረጠበት፣ ይልቁኑ ደግሞ በ1975 ኢ.ም. በድጋሚ የዚሁ ኮሚቴና የፖለቲካ ቢሮ አባል ሆኖ ከተመረጠ ወዲህ የትግራይን ህዝብና የኢትዮጵያን ህዝብ ትግል ትርጉም ባለው ሁኔታ ወደፊት ያራመዱ የፖለቲካ ተቋሞች እንዲነደፉ እጅግ የላቀ አስተዋፅኦ አድርጓል፡፡


Meles Zenawi at work during the liberation struggle days

የመለስ ባለራዕይነት፣ የለውጥ አንቀሳቃሽነትና መሪነት ጎልቶ በየመድረኩ ለሚነሱት የፖለቲካ ጥያቄዎች በጥናት ላይ የተመረኰዙ ትንተናዎችና ወደ ተጨባጭ የተግባር መመሪያነትም ሊሸጋገሩ የሚችሉ አቅጣጫዎች በማስቀመጥ ብቃቱ ጎልተው ታይተዋል፡፡ ከዚህም አኳያ በትግራይ ህዝብ ላይ የተጫኑት በደሎች በአስተማማኝ ሁኔታ ሊወገዱ የሚችሉት በኢትዮጵያ ህዝባዊ ዴሞክራሲያዊ ስርአት ሲገነባ እንደሆነ፣ ለዚህም በአገር አቀፍ ደረጃ የዴሞክራሲያዊ ሀይሎች ህብረት ሊመሰረት እንደሚገባ አጥብቆ ሞግቷል፡፡

ህዝባዊ ወያነ ሓርነት ትግራይ (ህወሓት) በ1967 ተመስርቶ በትግል ላይ በቆየባቸው ቀጣይ 10 አመታት ውስጥ ምንም እንኳን እጅግ አስቸጋሪ ሁኔታዎችን አልፎ ህልውናውን ቢያረጋግጥም ትግሉ ወደፊት የመራመዱ ሁኔታ እጅግ አሳሳቢ ሆኖ ነበር፡፡ በዚህ ወቅት፣ በኢትዮጵያ ህዝባዊ ዴሞክራሲያዊ አብዮት ግቦች፣ የትግል ስትራቴጂና ታክቲኮች እንዲሁም የሀይሎች አሰላለፍ፣ ትጥቅ ትግሉ በመሀል አገር የሚገኙ ህዝቦችን አንገብጋቢ ጥያቄዎች መሰረት አድርጎ አድማሱን ስለሚያሰፋባቸው አግባቦች ግልፅ አቅጣጫን አስቀምጧል፡፡ ከዚህም በተጨማሪ ህወሓትም ሆነ ሌሎች የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ሀይሎች ሊከተሏቸው ስለሚገባቸው የድርጅት መልኰች ንድፍ ሲዘጋጅ መለስ የተልዕኰውን ከፍተኛውንና ወሳኙን ሸክም ተሸክሞ በውጤት አጠናቋል፡፡

በወቅቱ የትግል አጋሩ የነበረው የኢትዮጵያ ሕዝቦች ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ ኢህዴን(ብአዴን) ዙሪያ መለስ ጥንካሬ ይጐናፀፍ ዘንድ ህወሓት በሁሉም መስኮች ለራሱ የሚሰጠውን ያህል ትኩረት ሰጥቶ ሊደግፈው እንደሚገባ ግልፅና ወደ ተጨባጭ ተግባር የተሸጋገረ ጽኑ አቋም አራምዷል፡፡ በተጨማሪም ሌሎች ዴሞክራሲያዊ ድርጅቶች እንዲፈጠሩ ህወሓት በትጋት መንቀሳቀስና ማገዝ እንደሚኖርበት አበክሮ ለማስጨበጥ ሰርቷል፡፡ ይህም ወደኋላ በተግባር ተፈፅሟል፡፡

መለስ የኤርትራ ጥያቄ የኤርትራን ህዝብ የራስን ዕድል በራስ የመወሰን መብት በማክበር እልባት ማግኘት አለበት የሚል ከዚህ በፊት ማንኛውም የኢትዮጵያ ፖለቲካ ሃይል ያልያዘውን አቋም በድፍረት አራምዷል፡፡ በኋላም የኤርትራ ድርጅቶች በፖለቲካዊ ባህርያቸው ምክንያት የኤርትራን ህዝብ

ዴሞክራሲያዊ መብቶች ሊያረጋግጡ የማይችሉ፣ በኢትዮጵያ ህዝብ ትግልም ላይ ዴሞክራሲያዊ አቋም ለመያዝ የሚያስችል ተፈጥሮ የሌላቸው ድርጅቶች ናቸው የሚለው የህወሓት አቋም ይፋ እንዲሆን በማድረግ በዚህ ዙሪያ በድርጅቱ ውስጥ የነበረውን የተምታታ አስተሳሰብ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ አስተካክሏል፡፡ ይህ አቋምም የድርጅቱ የውጭ ጉዳይ መርሆ በምን አግባብ መቃኘት እንዳለበት መሠረታዊ ንጣፍ ሆነ፡፡

መለስ ምንጊዜም በመሠረታዊ ሃሳብና በጥብቅ መርሆ ቢመራም ሀሳቦቹ በተግባር መዋላቸውን ለማረጋገጥ የአገሪቱም ሆነ የዓለም ሁኔታ ከሚፈቅደው ጋር ለማጣጣም ገገር ሃሳብና መርሆ የሚጠይቀውንና ተጨባጩ ሁኔታ የሚያስገድደውን በሆደ ሰፊነትና በዘዴ ያስታርቃል፡፡ ለምሳሌ፡- ከአጋሮች ጋር በሚካሄድ ድርድር እነሱ የማይቀበሉትና የማይፈልጉት ካለ "አከራካሪውን ወደ ጐን አድርገን በምንስማማበት በትብብር እንስራ" በማለት ልዩነት ተከብሮ መደጋገፍ፣ መተባበር እንዲቀጥል መንገድ ያመቻቻል፡፡

ትግሉ ከሞላ ጐደል የመቆም አደጋ ተጋርጦበታል በተባለበት በ1977 መላውን የትግራይ ታጋይና ህዝብ እንዲሁም ከጐኑ የቆሙ ሌሎች ታጋይ ዴሞክራቶችን ራሳቸውን እንዲያበቁ፣ መድረኩ የሚጠይቀውን አስተሳሰብ እንዲጨብጡ፣ ለማስተማር ለማብቃት፣ ለማደራጀትና ለማሰማራት ሌት ከቀን ይደረጉ በነበሩ ጥረቶች ሁሉ መለስ እጅግ የላቀ ሚና ተጫውቷል፡፡ መለስ ይህንን ተልዕኮ በብቃት ለመወጣት የቻለው የትግሉን የጉዞ አቅጣጫ፣ ግቦችና መዳረሻዎች በጠራ ሁኔታ መገንዘብ ይችል ዘንድ፣ የአገራችንን ተጨባጭ ሁኔታ አልፎም በአውሮፓ፣ በኤስያና በአፍሪካ የተካሄዱ አብዮቶችን ባህርይና አካሄድ፣ በድል የተጠናቀቁትም ሆነ የተሰናከሉት ለድሎቻቸውና ለውድቀቶቻቸው የነበሩትን ምክንያቶች ሌት ተቀን በማጥናቱና በመመራመሩ፣ ያወቀውንም የለውጥ መሳሪያ ለማድረግ ከልብ የመነጨ ፍላጐትና ጥረት፣ ይህንንም የማድረግ ብቃት ስላለው ነው፡፡

የመለስ ባለራዕይነት የለውጥ ጠንሳሽና አንቀሳቃሽነት የታየበት ሌላው ታላቅ አብነት በ80 እና በ81 የተካሄደው የለውጥ እንቅስቃሴ ነው፡፡ ይህ ወቅት የኢትዮጵያ አብዮት ወደ ቀጣዩ የትግል መድረክ ለመሸጋገር የሚያኰበኩብበት ወቅት ነበር፡፡ የአብዮቱ ቁልፍ ጥያቄዎች ዝርዝር ምላሽ ይጠይቁ ነበር፡፡ እናም መለስ የዴሞክራሲና የብሄር ጥያቄ በኢትዮጵያ አብዮት፣ የመንግስት ስልጣንና የኢትዮጵያ አብዮት፣ የመሬት ጥያቄና የኢትዮጵያ አብዮት በሚሉና በኤርትራ ህዝብ የነፃነት ንቅናቄን በሚመለከቱ ጉዳዮች ላይ እጅግ ጥልቅ ትንታኔ የሰጠባቸውን የመወያያ መፃህፍት አዘጋጀ፡፡ የትግሉ ጐዳና በጠሩ መስመሮች ዙሪያ ግልጥልጥ ብሎ መታየት የሚችልባቸውን ንድፈ ሃሳባዊና ተግባራዊ ሀሳቦች ቀመረ፡፡ የኢትዮጵያ ህዝቦች አብዮታዊ ዴሞክራሲያዊ ግንባር (ኢህአዴግ) በህወሓትና በኢህዴን እንዲመሰረት የማዕዘን ድንጋይ የሆኑትን ሃሳቦች አነጠፈ፡፡ ከዚህ በኋላም ህወሓትና ኢህዴን ኢህአዴግን እንዲመሰርቱ በስትራቴጂያዊ ማጥቃቱ ዋዜማም የኦሮሞ ህዝብ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት (ኦህዴድ) ተመስርቶና የኢህአዴግ አካል ሆኖ እንዲጓዝ መለስ የላቀ ሚና ተጫውቷል፡፡

መለስ ሌላ ታላቅ አስተዋፅኦ ያደረገበት ቁልፍ ጉዳይ የኢህአዴግ የወታደራዊ አስተምህሮ (ዶክትሪን)፣ እንዲሁም ሳይንስና ጥበብ ምን መምሰል እንዳለበት ያቀረበው ንድፍ ነው፡፡ መለስ በዚህ ንድፉ ጦርነት ሳይንስ እንጂ በእድል ላይ የሚመረኰዝ ያለመሆኑን፣ በታቀደና በተጠና አግባብም መፈፀም እንዳለበትና ማንኛውም የውትድርና ተግባር ፖለቲካዊ አላማውን የሚያገለግል እንዲሁም ሕዝቡንም ዋነኛ

ኃይል አድርጎ በባለቤትነት የሚያሳትፍ ሊሆን እንደሚገባው ተንትኗል፡፡ የዚህ መስመር ትክክለኛነትም ኋላ በተደረጉ ውጤታማ ጦርነቶች በተግባር ተረጋግጧል፡፡

መለስ በስትራቴጂያዊ ማጥቃቱ ዋዜማ ባቀረበው "ሳይንሳዊ ትንበያ" በስትራቴጂያዊ ማጥቃቱ ሊከተሉ የሚችሉትን ሶስት መጪ ግምታዊ ሁኔታዎች (scenarios) ከሩቁ ተመልክቷቸዋል፡፡ በዚህ ብዙዎችን ባስደመመ ትንተና ያስቀመጣቸው መጪ ግምታዊ ሁኔታዎች አንደኛ፡ ደርግ ሙሉ በሙሉ ተወግዶ በኢህአዴግና በሌሎች የፖለቲካ ኃይሎች ስምምነት የሚፈጠር የሽግግር መንግስት፤ ሁለተኛ፡ ደርግ በዋነኛነት ኦሮሚያንና ደቡብን ተቆጣጥሮ ትርጉም ያለውን ሀይሉን ይዞ የሚቆይበት እና ሶስተኛ፡ ደርግንና ኢህአዴግን ያካተተ የሽግግር መንግስት የሚቋቋምበት ብሎ በመለየት የሁሉንም ሁኔታዎች ባህርይ በመተንተን፤ የሽግግሩ ወቅት በምን አግባብ ሊሆን እንደሚችል ለመተለም ችሏል፡፡ የሽግግሩ መንግስት ምስረታ ከሞላ ጐደል በደርግ ሀይል ውድቀት ላይ ይመሰረታል ተብሎ በመገመቱም መለስ የሽግግሩን ወቅት ባህርይ የሚገልፅ ሰነድ ሰርቷል፡፡ ይህ ሰነድም በደርግ ውድቀት ዋዜማ አንድ ትልቅ የትግል ሰነድ በመሆን አገልግሏል፡፡

መለስ ዜናዊ የደርግ መንግስት መውደቅ እየተቃረበ መምጣቱ ገሃድ በሆነበት በ1981 ዓ.ም መጨረሻ አካባቢ ጀምሮ በኢህአዴግ ይነሳ የነበረውን የአብዮቱን ያለመመጣጠን ጥያቄ ለመፍታት መወሰድ የሚገባቸውን ርምጃዎች በመቀየስ ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል፡፡ ህዝባዊ ትግሉ ከታጠረበት ከሰሜን ኢትዮጵያ በመውጣት ወደ መሃል አገርና ወደ ደቡብ፣ ምዕራብና ምስራቅ ኢትዮጵያ እንዲስፋፉ፣ በነዚህ አካባቢዎች ደርግን እየተዋጉ ከሚገኙ ድርጅቶችም ጋር ግንኙነት እንዲፈጠር ቁርጠኛ አመራር ሰጥቷል፡፡

መለስ ደርግ ሊወድቅ ጥቂት ወራት በቀሩት ጊዜ ከደርግ ውድቀት በኋላ ኢህአዴግ ለአንድ ወር ብቻ የሚቆይ ጊዜያዊ መንግስት እንደሚያቋቁም አመላከተ፡፡ በዚህ ጊዜ ውስጥ በኢትዮጵያ ውስጥም ሆነ በውጭ አገር የሚኖሩ የደርግን አገዛዝ እንታገላለን ብለው የተደራጁ ፖለቲካዊ ድርጅቶች፣ ሲቪክ ማህበራት፣ የደርግ መውደቅ የሚፈጥርላቸውን እድል በመጠቀም ተደራጅተው የሚመጡ ሃይሎችን በሙሉ የሚያሳትፍ፤ ሁሉም አይነት ፖለቲካዊ አስተሳሰቦች በነፃ የሚደመጡበትና አዲሲቱን ኢትዮጵያ የመገንባት ሃላፊነት የሁሉም ኢትዮጵያዊ ድርሻ መሆኑ በተግባር የሚረጋገጥበት የሽግግር መንግስት እንደሚመሰረት አብራራ፡፡ የሽግግር መንግስቱም እድሜ ከሁለት እስከ ሶስት አመት ብቻ እንደሚሆንና በዚህ ጊዜ ውስጥ የመላ ኢትዮጵያ ህዝቦችን ነፃና ቀጥተኛ ተሳትፎ በሚያረጋግጥ አግባብ ህገ-መንግስት አዘጋጅተንና አፅድቀን አገራዊ ምርጫ በማድረግ ዴሞክራሲያዊ መንግስት እናቋቁማለን የሚል ግልፅ አቋም አቀረበ፡፡ ይህ አቋምም ውሎ ሳያድር የኢህአዴግ አቋም በመሆን ስራ ላይ ዋለ፡፡ ያኔ በቦታው የነበሩ አንዳንድ ድርጅቶችና የውጭ ኃይሎች "እናንተ ይህንን ያህል አመት በደማችሁትና በታገላችሁት ለምን ሌሎችን ትጋብዛላችሁ፤ ምን የሚረባ ድርጅትስ አለና" የሚል "ምክር ለመለገስ ሞክረውም ነበር፡፡ መለስ ይህንን ምክር ባለመቀበል ለመርህ የቆመ፣ የሚያምንበትንም መርህ መቸም ይሁን የትም በግልፅ ከማራመድና ተግባር ላይ ከማዋል ወደ ኋላ የማይል መሆኑን አረጋግጧል፡፡

ከ80ሺ.ህ በላይ ቁጥር ያለውና በከፍተኛ ወታደራዊ ብቃት የተገነባ ሰራዊት የያዘው ኢ.ህአዴግ ያለአንዳች አለሁ ባይ አገሪቱን መቆጣጠር እንደሚችል መገመት ባይከብድም መለስ ግን በጭራሽ አይቻልም፣ ቤተመንግስትን ብንቆጣጠርም የመላ ኢትዮጵያን ህዝቦች ልቦና ልንቆጣጠር አንችልም፡፡ የአገራችንን ብዙሕነት በአግባቡ የሚያስተናግድ፣ ሁሉንም ፖለቲካዊ ሃይሎች የሚያሳትፍና የኢትዮጵያ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ፈቅደው በመዋሃድ አዲሲቱን ዴሞክራሲያዊት ኢትዮጵያ እንዲገነቡ በብቃት የሚያዘጋጅ የሽግግር መንግስት ካልመሰረትን ስልጣን በያዝን ማግስት ወደ ሌላ ጦርነት መግባታችን፣ አገራችንም የነዩጎዝላቪያ እጣ እንደሚገጥማት አይጠረጠርም በማለት ሞገተ፡፡ እናም አገራችን ዛሬ ለደረሰችበት የእድገትና ትራንስፎርሜሽን መድረክ እንድትበቃ ያደረገ ጠንካራ መሰረት እንዲጣል መለስ ግንባር ቀደሙን ሚና ተጫውቷል፡፡

ብሩሁ የመለስ አእምሮ የኢትዮጵያ መፃኢ እድል በየትኛው የትግል መስመር ላይ ይመርኮዝ የሚለውን ሃሳብ ከማውጠንጠን አርፎም አያውቅም፡፡ ሀገር አቀፍና ዓለም አቀፍ ሁኔታዎችን ግምት ያስገቡ የትግል መስመሮች እንንደፍ በማለት፣ አማራጫችን በኢኮኖሚ መስክ መላው ህዝብ በየደረጃው ተጠቃሚ የሚሆንበት የነፃ ገበያ ኢኮኖሚ ግንባታ መመስረት፣ በፖለቲካ መስክ የመድበለ ፓርቲ መመስረት፤ የሚሉት ሃሳቦች ከበፊቱ ፊታ ብለው ተቀመጡ፡፡ ሰላም፣ ዴሞክራሲና ልማት የማይነጣጠሉ የህልውናችን መሰረቶች ናቸው ተብሎ ተነደፈ፡፡ መለስ የዚህ አስተሳሰብ ግንባር ቀደም አራማጅ ነው፡፡

ኢትዮጵያ ካልለማች በድህነት ትበታተናለች፤ በፍጥነት እንልማ፤ ያለሰላም ልማት አይኖርም፤ ሰላማችንን አስተማማኝ ለማድረግ ህዝቡን የልማት ተጠቃሚ እናድርገው፤ ያለዴሞክራሲ ልማት የለም፤ ዴሞክራሲው በሰፊ ህዝባዊ ተሳትፎ ላይ ይመስረት፤ ጥቂት ባለስልጣኖች ብቻ ሳይሆኑ ከቀበሌ እስከ ሀገር አቀፍ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ የህዝብ ተወካዮች ይኑሩን በማለት አጥብቆ አስተምሯል፡፡ የኢትዮጵያ ህዝቦች ለዘመናት የነበረውን መጥፎ ቅርስ ሽረው ተከባብረውና ፈቅደው አንድ የጋራ የኢኮኖሚና የፖለቲካ ማህበረሰብ ለመመስረት ያለሙበት፤ ዴሞክራሲያዊ ህገ-መንግስት ረቂቅ ዝግጅት ላይ መለስ ቀዳሚ መሰረት ጣይ በመሆን አመራሩን በብቃት ተወጥቷል፡፡

እስከ 90ዎቹ መጀመሪያ በነበሩት አመታት ሀገራችን ከነበረችበት አዝጋሚ ጉዞ አልወጣችም ነበር፡፡ ከሁሉም በላይ ደግሞ በኢ.ህአዴግ ውስጥ እያቆጠቆጠ የመጣው የጥገኝነት አስተሳሰብ ለመለስ እጅግ አሳሳቢ ጉዳይ ሆነ፡፡ መለስ ስልጣንን መንታ ስለት ያለው ካራ ነው በማለት ይገልጸዋል፡፡ ይህ ካራ ወይ ድህነትን አለያም ህዝብን ለማረድ ሊውል ይችላል ይላል፡፡ የያዝነው ስልጣን ራሳችንን ወደ ገዢ መደብ የምናሸጋግርበት፣ ሀብት ንብረት የምናፈራበትና ወገን ዘመዶቻችንን የምንጠቅምበት መሳሪያ ሳይሆን ህዝብን የምናገለግልበት የትግል መሳሪያ ነው፡፡ ስለዚህም መክበር የሚፈልግ ሰው ቦታው ኢ.ህአዴግ አይደለምና የገዢ መደብ አመለካከትን አጥብቀን መታገል አለብን በማለት በጽናት ሞግቷል፡፡ ውስጣችን እየተበላሸ በሄደ ቁጥር ጉዞው መደነቃቀፍ ይበዛበታል፤ መጨረሻም ተሰናክለን እንወድቃለን፣ ድርጅታችን፣ መንግስታችንና ሀገራችን በቀላሉ ወደማያገግም ውድቀት እንዳይገቡ እንታደስ፣ አዳዲስ አስተሳሰቦችን እንላበስ፣ ወቅቱ ከሚጠይቀው አዲስ አስተሳሰብ ጋር ተዳብለው የተያዙትን ነባር ድሪቶ አስተሳሰቦች እናራግፋቸው በማለት የተሃድሶ መስመሮችን ለመንደፍ ማጥናት መመራመሩን ተያያዘው፡፡

መለስ ይህንን አድካሚ ጥናት ካጠናቀቀ በኋላ ዝርዝር ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች ነድፎ በኢህአዴግ አመራር እንዲተችባቸውና እንዲዳብሩ ካደረገ በኋላ መላው ታጋይና ህዝብ እንዲጨብጣቸው ለማድረግ ሰራ፡ ፡ ከዚህ ጉዞ በስኬት መጠናቀቅ በኋላም በ1994 ዓ.ም በተካሄደውና የ"እመርታ" ጉባኤ ተብሎ በሚታወቀው ጉባኤ አማካይነት የድርጅቱ ኋላም የመንግስት መመሪያዎች  እንዲሆኑ በማድረግ የህዳሴውን ንቅናቄ መምራት ጀመረ፡፡

የመለስን ባለራዕይነትና የለውጥ ፈላጊነት የሚያመላክተው ሌላው ትልቁ አብነት ኢትዮጵያን በቀጣዮቹ አሰርት ዓመታት የበለፀጉ ሀገሮችን ጐራ እንድትቀላቀል ያስቀመጠው ራዕይ ነው፡፡  ይህ ራዕይ ኢትዮጵያ ካለችበት የድህነት ሁኔታ በተሟላ ደረጃ  የምትላቀቅበትና የዳበረ ኢኮኖሚና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ባለቤት የምትሆንበት ራዕይ ነው፡፡  የእድገትና የትራስፎርሜሽን ዕቅዱም የዚሁ ራዕይ አካል ነው፡፡ ይህ ዕቅድ የኢትዮጵያን ማህበረ-ኢኮኖሚ መዋቅር ወደ ኢንዱስትሪ መርነት እንዲሸጋገር የሚያስችለውን ሁኔታ የሚፈጥር ነው፡፡  ብዙዎች የዚህን የእድገትና የትራንስፎርሜሽን እቅዱን ከፍተኛው ግብ ቀርቶ መሰረታዊ ግቡ እንኳ ይፈፀማል ብለው ለማስቀመጥና ለማመን አይደፍሩም፡፡

## መለስ፡ በውሱን ውጤት የማይረካ ታላላቁን የሚመኝ፣ የሚደፍርና የሚያደፋፍር መሪ !

መለስ የህዳሴው ጉዞ ከተጀመረ በኋላም በተለይም በመጀመሪያዎቹ ሁለትና ሶስት አመታት በተገኙት ለውጦች አልረካም፡፡ የልማቱ ፍጥነትና ስፋት ሁሌም እንዳሳሰበው ነበር፡፡ በገጠር የተገኙትን መልካም ውጤቶች በላቀ ፍጥነትና ጥራት ካላስፋፋን፣ ወደ ኋላ የቀሩትን ከተሞቻችንን ተአምራዊ ስራ ሰርተን ገለባብጠን ካላሻሻልናቸው፣ ባስቀመጥናቸው አዳዲስ መስመሮችና አሰራሮች ድርጅታችንን ሙሉ በሙሉ ካላደስነው፣ የወጣቶችንና የሴቶችን ችግሮች ቀልጥፈን ካልፈታን፣ ወጣቶችን ከድርጅታችን ጎን በሚሊዮኖች አሰልፈን መልካም ተመክሮዎቻችንን አጋርተን የትግሉ ዋነኛ ባለቤቶች ካላደረግናቸው አስቸጋሪ ሁኔታ ይፈጠራል፣ እንፍጠን! ነበር የዘወትር ሃሳቡና የስራውም መመሪያ፡፡



ታላቁ መሪ በአንድ ወቅት የሀገራችንን የድህነት ሁኔታና የርምጃችንን ፍጥነት እጅግ በሚያስገርም የንጽጽር አገላለጽ እንደሚከተለው አስቀምጦት ነበር፡፡ የኛ ጉዞና ከተራራ ጫፍ የሚወርድ ናዳ  ይመሳሰላሉ፡ ፡ ከላይ ከሚወርድ ናዳ ለማምለጥ የሚሮጥ ሰው ከናዳው የላቀ ፍጥነት ከሌለው ናዳው በጀመረበት የመጀመሪያም ሆነ በመጨረሻው ሰአት ላይ ቢሞት ያው ሞቷልና በመጀመሪያውም ሆነ በመጨረሻው ሰዓት መሞቱ ትርጉም የለውም፣ ስለዚህም ሀገራችንን መንግስታችንንና ድርጅታችንን ሊበታትን ከሚችለው ናዳ እጅግ በላቀ ሁኔታ መፍጠን ይገባናል፡፡ ስለዚህም የመለስ የርብርብ ማዕከል የስራ ጥራት፣ ፍጥነትና ስፋት ነበሩ፡፡

መለስ ሁሌም ከቁጥ ቁጥ አሰራር እንውጣ፤ በትንንሽ ውጤቶች አንርካ፤ በስፋት እናቅድ፤ ታላላቅ ስራዎች እንስራ፤ ከዚህም ከዚያም አጠረቃቅመንና ክራባት ለብሰን እየለመንን ያገኘነውን ሀብት አግባብ ባለው ሁኔታ አብቃቅተን እንጠቀምበት፤ ህዝባችንን ሁሌም ተጠቃሚ እናድርገው፤ እናዳምጠው፤ ሲያርመን እንስማው፤ ትክክሉን እንውሰድ፣ ሲሳሳት እናስተምረው፤ ካልሰራንለትና ካልሰማነው "ጨው ለራስህ ስትል ጣፍጥ አሊያ ድንጋይ ነው ብለው ይወረውሩሀል" ነበር ምሳሌው፡፡

ለመለስ ከድህነት በላይ አዋራጅ ነገር የለም፤ በድህነት የተቆራመዱና ጠኔ እየገረፋቸው የሚኖሩ፤ የሚለብሱት አጥተው በእርዛት የሚቸገሩና በመጠለያ እጦት ምክንያት ባረጁ ጐጆዎች ተጨፋፍቀው የሚያድሩ ዜጐች ሀገር ይዘን እንቅልፍ ተኝተን ልናድር አይገባንም፡፡ ስለዚህም ጠላታችን የሆነውን ድህነትን በማጥፋት ዜጐቻችንን ሰብአዊ ክብር ማላበስ፤ ሀገራችንንም ከተስፈኞች ጐራ ማውጣት አለብን የሚል ፅኑ አቋም ነበረው፡፡ ከዚህ አኳያ የሀገራችን እድገት ጐልቶ እንዲታይ ያደረጉት የከተማና የገጠር ልማት ፖሊሲዎች የአፈፃፀም ሥልቶች በምሳሌነት ይጠቀሳሉ፡፡

ከገጠር ልማት አኳያ በነደፈው የገጠር ልማት ስትራቴጂ ላይ ዋነኛ አቅሞቻችን ናቸው ያላቸውን የአርሶ-አደሩን ጉልበት፣ መሬትና ውሃ በአግባቡ አቀናጅቶ በመጠቀም በአርሶ አደሩ ማሳዎች ላይ የግብርና ምርትና ምርታማነት በላቀ ደረጃ እንዲያድግ ያላሰለሰ ብቁ አመራር ሰጥቷል፡፡ ከዚህም አልፎ አርሶ አደሩ ከእጅ ወደ አፍ ከሆነ ምርት ተላቆ ወደ ገበያ የሚቀርብ ምርት እንዲያመርት ያስቻለ አቅጣጫ ነድፎ ተግብሯል፡፡ አርሶ አደሩንና የምርቱን ተጠቃሚዎች ከአቀባባዮች ብዝበዛ ለማላቀቅ ዓላማ ያለመና በገጠርም በተስፋፋው የቴሌኮም አገልግሎት የታገዘ የግብይት ስርአት እንዲፈጠር የላቀ አመራር ሰጥቷል፡፡

ምርጥ የተባሉትን የውጤት ተመክሮዎች ለቅሞ በመያዝና እነርሱንም በማስፋፋት አላማ፤ ከክልል ፕሬዝዳንቶችና የግብርና ቢሮ ሃላፊዎች ጋር ቋሚ የግንኙነት ስርአት በመፍጠር የደከሙት ከተሻሉት እንዲማሩና የተሳካላቸው ገበሬዎችና የልማት አስፈፃሚዎች እውቅና የሚያገኙበት ስርአት እንዲፈጠር ለማድረግ ያስቻለን የአመራር ጥበብ ተፈፃሚ አድርጓል፡፡ በዚህ ታላቅ ጥረቱም ዛሬ በቀን ሁለት ሦስቴ የሚበሉ በርካታ ሴቶችን ጨምሮ በሀገራችን በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ አርሶ አደሮች ተፈጥረዋል፡፡ ተያይዞም የአርብቶ አደሩን ሕይወት ለማሻሻል የውሃ አጠቃቀምና የእንስሳት ልማትን ለማዳበር በተለይም የእንስሳትን ጤና፣ መኖና የግብይት ሥርዓትን ለማሻሻል እንዲሁም አርብቶ አደሩ በፍላጐቱ ሰፍሮ የተረጋጋ ኑሮ እንዲመራ ለማድረግ የሚያስችል የአርብቶ አደር አካባቢዎች ልማት ፖሊሲና እስትራቴጂ ቀርጾ እንዲተገበር ብቁ አመራር ሰጥቷል፡፡

መለስ በከተሞች የሚታየውን የወጣቶችና የሴቶች ድህነት ለመፍታትና ከዚህም ዓላማ ጋር አቆራኝቶ ከተሞችን ለማልማት ልዩ ትኩረት ሰጥቷል፡፡ ወጣቶችና ሴቶች ቀልጥፈው ገቢ የሚያገኙባቸውን የልማት ፓኬጆች በመለየት መነሻ የስራ ካፒታል በብድር እንዲያገኙ፣ እንዲሁም የሙያ ሥልጠና፣ የማምረቻና የመሸጫ ቦታዎች እንዲመቻቹላቸውና የገበያ ትስስሮች እንዲፈጠሩላቸው ያላሰለሰ ጥረት አድርጓል፡፡ በዚህም በርካታ ወጣቶች እና ሴቶች ከድህነት ተላቀዋል፡፡

ከተሞች የሀብታሞች ብቻ ሳይሆኑ ዝቅተኛ ገቢ ያላቸው ዜጎች ተመችቷቸው የሚኖሩባቸው ማዕከላት መሆን እንዳለባቸው በፅናት ለማስጨበጥና ለማስፈፀም ታግሏል፡፡ በዚህም መሠረት በመንግስት የቤቶች ልማት ፖሊሲ አማካይነት ነዋሪዎች የመኖሪያ ቤት ባለቤቶች እንዲሆኑ የላቀ ሚና ተጫውቷል፡፡ ነዋሪዎች ቤትን በመጠለያነቱ እንዲያገኙት ብቻ ሳይሆን ይህንን ችግር ከመፍታት ጎን ለጎን ሁለት አላማዎች ተቆራኝተው መፈፀም እንዳለባቸው በግልፅ ነድፏል፡፡ ይኸውም ቤቱ የኔ ነው ብለው በባለቤትነት እንዲይዙት በማድረግ የሀብትን ፍትሐዊ ሥርጭት ማረጋገጥና በቤት ልማት ዙሪያ የሥራ እድል መፍጠር ናቸው፡፡ ድሃ ተኮሩ የጥቃቅንና አነስተኛ ተቋማት ልማትና የቤቶች ልማት ፖሊሲው በሌሎች ታዳጊ ሀገራትም የተደነቀና በተመክሮነትም የሚወሰድ ፍጻሜ እንዲሆን መለስ ብቁ አመራር ሰጥቷል፡፡

የአገራችን ልማታዊ ባለሀብቶች ከባእድ ባለሀብቶች ቅድሚያ አግኝተው በአገሪቱ ልማት ውስጥ የድርሻቸውን እንዲያበረክቱ በማበረታታትና ተገቢ የፖሊሲ ማዕቀፎችን በመንደፍ መለስ አኩሪ የመሪነት ሚና ተጫውቷል፡፡ በዚህም መሠረት በሀገር ውስጥ ከተፈጠሩት ልማታዊ ባለሀብቶች ባሻገር ትውልደ ኢትዮጵያዊያን በሀገራቸው የልማት ግስጋሴ ላይ ያካበቱትን እውቀትና ሀብታቸውን ተጠቅመው የድርሻቸውን እንዲያበረክቱ አስችሏል፡፡

መለስ በውስን ግብና በመጠነኛ ውጤት የማይረካ፣ ታላላቁን የሚመኝ የሚደፍርና የሚያደፋፍር መሆኑ በግልፅ የታየበት ሌላው ታላቅ አብነት የታላቁ የህዳሴ ግድብ እቅድ ነው፡፡ ሌሎች ሊፈፅሙት ይቅርና ሊያስቡትም የማይደፍሩትን በአባይ ወንዛችን ላይ ከአፍሪቃ በትልቅነቱ ቀዳሚ የሆነውን ታላቁን የህዳሴ ግድብ የመገንባት እቅድ አረቀቀ፡፡ ለግድቡ ግንባታ ከፍተኛ ገንዘብ እንደሚጠይቅና ይህንንም ከውጭ ብድርና እርዳታ ማግኘት እንደማይቻል ቢገነዘብም፣ የሀገራችን ሕዝቦች የቆየ ቁጭትና የልማት ቀናኢነት ከፍተኛ ሃብት መሆኑን የሚያስገነዝብ፣ አርቆ አስተዋይነት የተመላበትና ቁርጠኛ አቋም ያዘ፡፡ በሕዝቡ ውስጥ የነበረውን አይቻልም የሚል አስተሳሰብ የሰበረና ቀድሞ የነበሩ የኢትዮጵያ መንግሥታት ያልደፈሩትን የደፈረ የክተት አዋጅ በአይቻልም ባይነት ላይ አወጀ፡፡

የመለስ የአስተሳሰብና የድርጊት መርሆ ማዕከላዊ ነጥብ ድሪቶ መጣፍ ሳይሆን አዲስ አስተሳሰብ ማላበስ፣ ድህነትን መግታትና ደሀውን ከክፉ እልቂት መመከት ሳይሆን ድህነትን መርታትና በድህነት ለዘመናት ተጠምዶ የማቀቀውን ሕዝብ የብልፅግና ምንጭ እንዲሆን ማብቃት ነው፡፡ ቀዳማዊ ዓላማው የሚያስታግሰውን ሳይሆን፣ የሚፈውሰውን መሻት፡፡ የደከመው፣ የወደቀው፣ ለመትረፍ ከመፍጨርጨር አልፎ ኑሮውን አቸንፎ ምኞቱ ለወገኑና ለአገሩ መድረስ እንዲሆን ማሳደግ ነው፡፡

## መለስ ለሃሳብ፡ ተግባር ላይ ለሚውል ሃሳብ የላቀ ትኩረት ይሰጣል!

መለስ ለሃሳብ ክርክር ትልቅ ቦታ ይሰጣል፡፡ በሚያቀርበው ሃሳብ ላይ በቂ ዝግጅት አድርጐ ይመጣል፡፡ እሱ ከሚያምንበት የተለየ ሃሳብ ሲቀርብ ትኩረት ሰጥቶ ያዳምጣል፡፡ የተሳሳተ ሃሳብ ነው ብሎ ካመነ ሊያሳምኑ የሚችሉ ሰፊ መረጃዎችንና ማጣቀሻዎችን በማቅረብ ያሳምናል፡፡ ማሳመን ካልቻለ የራሴ ድክመት ነው ብሎ ለቀጣይ ጥናትና ትንታኔ ራሱን ያዘጋጃል፡፡ እሱ ካቀረበው የተለየና የሚያሳምነው ሃሳብ ሲኖር ደግሞ ለመቀበል አያቅማማም፡፡ አምኖበት ስለሚቀበልም በይበልጥ ይተነትነዋል፡፡ በተግባርም ላይ እንዲውል ያዳብረዋል፡፡

ማንኛውንም ሃሳብ የሚመዝነው ምን ያህል በተግባር ላይ ይውላል ከሚል መነሻ ሲሆን ከተግባር ጋር የማይያያዝ፣ አንድም ችግር የማይፈታ የሃሳብ ክርክር ውስጥ አይገባም፡፡ የማንኛውም ሃሳብ ሚዛኑ ምን ያህል ለምናካሂደው ተግባር ያገለግላል የሚል ነው፡፡ ከተግባር ጋር የማይያያዝ የክርክር ሃሳብ ሲገጥመው “በአንድ የመርፌ አናት ላይ ስንት መላእክት ይጨፍራሉ” የሚል ክርክር ማድረግ የለብንም ይላል፡፡ በትግሉ፣ በድርጅቱና በአጠቃላይም በአገር ጉዳይ በሚኖሩ ውይይቶች ላይ መሪ ሃሳብ ይዞ ይቀርባል፡፡ ከአንድ ነጥብ በመነሳት ዙሪያ መለስ ጉዳዮችን የሚዳስስና የሚያብራራ ፅሁፍ በማቅረብ ድርጅቱ የተሟላ አቅጣጫ እንዲይዝ ያደርጋል፡፡

በትጥቅ ትግሉ ወቅት በህወሓት አመራር ውስጥ የተነሱ የሃሳብ ልዩነቶችን መሰረት በማድረግ የኢትዮጵያ አብዮትን መሰረታዊ ፖለቲካዊ ጥያቄዎችና የኤርትራን ህዝብ ትግል የሚመለከቱ መፃህፍት ፅፏል፡፡ በነዚህ ፅሁፎቹ ሌሎች ያነሱት ሃሳብ ለምን ስህተት እንደሚሆን፣ ትክክለኛው ሃሳብ ከንድፈ-ሃሳብ፣ ከታሪክና ካለንበት ተጨባጭ ሁኔታ አኳያ እንዴት ሊታይ እንደሚገባ የሚተነትንና እንዴት ስራ ላይ ሊውል እንደሚችል ዝርዝር የአፈፃፀም አቅጣጫዎችን የሚያስቀምጥ ነበር፡፡ በመድረክም ላይ ሲከራከር የግለሰቦችን ሃሳብና የግለሰቦቹን ሰብዕና ለይቶ በሚያቀርብና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ነበር፡፡ በ1993 ዓ.ም. በተካሄደው የድርጅቱ የተሃድሶ እንቅስቃሴም በድርጅቱ ውስጥ ለሚታዩት ችግሮች በጥናት ላይ በመመስረት ሰፊ መወያያ ፅሁፍ ያዘጋጀ ሲሆን፤ ሌሎች የአመራር አባላት ያነሱዋቸውን ሃሳቦች መሰረት በማድረግም አንድ ወር ባልሞላ ጊዜ ውስጥ በአማካይ እስከ 150 ገፅ ያላቸው 3 ፅሁፎችን በማቅረብ የተሃድሶው እንቅስቃሴ በጠራ አስተሳሰብ እንዲመራ ግንባር ቀደም ሚና ተጫውቷል፡፡

መለስ ሃሳብ ማፍለቅ፣ ከሌሎች የሚመጡ ሃሳቦችን በሃሳብ መሞገት፣ ለሌሎች ሃሳብ ክብር መስጠት ብቻ ሳይሆን የያዙትን ሃሳብ ወደ ተግባር በማሸጋገርም በኩል የሚደነቅ ችሎታ አለው፡፡ ሃሳብን በቀኖናነት አይመለከተውም፤ ሃሳብን የሚፈልገው ለተግባር መመሪያነት ነው፡፡ አንድ ተግባር ሲታቀድ፣ ተግባሩ የሚመራበትን ሃሳብ ወደማፍለቅና መተንተን ይገባል፤ ያቀረበውን ሃሳብ መሰረት በማድረግም ፈፃሚ አካላት ሁሉ በብቃት እንዲሰማሩ ያስተምራል፣ የተግባሩን አፈፃፀም በቀጣይነት ያረጋግጣል፡፡ በተፈፀመ ተግባር ላይ ተመስርቶ ሪፖርት ሲያቀርብም ሆነ ግምገማዎች ሲያካሂድ የተግባሩንና የሃሳቡን ጥምረት በአግባቡ ይመረምራል፡፡ ሲጠቃለል የሃሳብ ክርክርን ለህዝብ ካለው ጥቅም አኳያ ይመዝነዋል፡፡ ሃሳብን በሃሳብ ከማሸነፍ አማራጭ ውጪ ሌሎች አቅሞችን፣ መሳሪያዎችንና ዴሞክራሲያዊ ያልሆኑ አግባቦችን መጠቀምን አጥብቆ ያወግዛል፡፡

**በብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ነፃነት፣ እኩልነትና ዴሞክራሲያዊ አንድነት ፅኑ እምነት ያለው ሃገራዊ መሪ!**

መለስ ገና ከጠዋቱ አገራችን ኢትዮጵያ ብዙሃን ብሄሮችና ሃይማኖቶች ያቀፈች እንደመሆንዋ ልዩነታችንን አክብረን የተዘነጉ፣ የተናቁ ማንነታቸውና እኩልነታቸው እውቅና አግኝቶ የአገሪቷ ዲሞክራሲያዊ አንድነት ነፃና ሕያው አካል እንዲሆኑ በሰፊው ጥሯል፡፡ የአገሪቱ ዓብይ ኃይል አርሶና አርብቶ አደሩ ነውና የኢትዮጵያ የዲሞክራሲም ሆነ የልማት መሠረት ገጠሬው እንደሆነ አሳይቷል፡፡ ብዝሃነትን ማክበር የአገሪቱ ህልውና መሰረት መሆኑን አፅንኦት ሰጥቶ አስተምሯል፡፡ በገዛ አገራቸው ተዘንግተው የኖሩ፣ የተናቁና ማንነታቸውና እኩልነታቸው የተገፉ ወገኖች እኩልነታቸው ታውቆ በአገሪቱ ወሳኝ ተግባራት ተሳታፊና የውጤቱም እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ በዚህም የአገሪቱ ዴሞክራሲያዊ አንድነት ነፃና ህያው አካል እንዲሆኑ በሰፊው ተንቀሳቅሷል፡፡

ይህ እሳቤ ለትግሉ እርምጃ መስፋፋት፣ ለሽግግሩ ስምረት፣ ህገመንግስቱ የምልዓተ ህዝብ ተቀባይነት አግኝቶ እውን እንዲሆን ለማድረግ እንዲሁም የአገሪቱ ፖሊሲዎች የአገሪቱን ነባራዊ ገፅታ የሚያንፀባርቁ እንዲሆኑ ለማስቻል ዋነኛ ማጠንጠኛ ሆኖ እንዲያገለግል ለማድረግ መለስ በእጅጉ ተንቀሳቅሷል፡፡

መለስ የአገራችን ህዝቦች ከአንድ ውሱን አካባቢ በወጡ ገዢዎች ጭቆና ስር ሲማቀቁ እንደነበሩ፣ ያ አገዛዝ ለዛም አካባቢ ህዝብም ያልጠቀመ እንዲያውም እንደ ሌሎች ህዝቦች ሁሉ የግፉ ተሸካሚ እንደነበረ በማሳየት የአገራችንን ህዝቦች ሁሉ ትግል ለማስተባበር የሰራ፣ ትግሉን ከመላ የአገሪቱ ህዝቦች ጋር የአገሪቱን ብዙሃን ህዝቦችም ከትግሉ ጋር ያስተዋወቀና ያስተሳሰረ መሪ ነው፡፡

ኦነግና ሌሎች የፖለቲካ ሃይሎች ወደ ሽግግሩ መድረክ እንዲቀላቀሉና እንዲቀጥሉ መለስ በፅኑ ታግሏል፡፡ የተለያዩ የፖለቲካ ሃይሎች በሽግግሩ ውስጥ መካተታቸው ለአገራችን የዴሞክራሲ ስርአት ግንባታ፣ ለሰላምና ለመረጋጋት ይጠቅማል ከሚል እምነት በመነሳት አገሪቱን ወደ መድብለ ፓርቲ ስርአት ለመምራት መለስ ከልቡ ታግሏል፡፡

በመጨረሻዎቹ የትጥቅ ትግሉ ጊዜያት ከደርግ ጋር ይካሄድ በነበረው ድርድር ወቅት የኢህአዴግ ዋና ተደራዳሪ የነበረው መለስ በድርድሩ ላይ ህወሓት ብቻ ሳይሆን በወቅቱ ኢህዴን በመባል ይጠራ የነበረው ህብረ ብሄራዊ የኢህአዴግ አባል ድርጅት መሳተፍ አለበት በማለት የያዘው አቋም የመለስን አርቆ አስተዋይነት ያስመሰከረ ነበር፡፡ ደርግ የህብረ ብሄሩ ኢህዴን በድርድሩ ላይ መሳተፍ በመላ አገሪቱ ለተቀጣጠለው ዴሞክራሲያዊ ትግል እውቅና መስጠት ሆኖ ስለተሰማው ሊቀበል አልፈቀደም፡፡ በሌላ በኩል ህወሓት መላ የአገራችንን ህዝቦች በሚመለከት ጉዳይ ላይ ለብቻው መደራደር ከመርህ አኳያ ተገቢ አይደለም ሲል የያዘው አቋም የሌሎች ድርጅቶችን በነርሱም አማካይነት የህዝቦችን እኩልነት ያንፀባረቀበት መሰረታዊ አቋም ነበር፡፡

የአገራችን ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ህገመንግስት የመላ የአገራችን ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች የጋራ ቃልኪዳን ሆኖ እንዲፀድቅ ያለፉ ቁርሾዎችንና ጥርጣሬዎችን በሚያስወግድ መልኩ ጉልብቶ እንዲወጣ መለስ ያደረገው ተጋድሎ ለሃገራችን ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ያለውን ፅኑ ፍቅርና አክብሮት ያረጋገጠ ነው፡፡

በእኩልነት፣ በመከባበርና በመፈቃቀድ ላይ የተመሰረተ አንድነት ማስፈን ካልቻልን አንድ የጋራ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ማህበረሰብ መፍጠር የሚባል ነገር ህልም እንደሆነ መለስ በተደጋጋሚ ያስተምር ነበር፡፡

መለስ ለሁሉም ነው! መለስ የሁሉም ነው! ለአገራችን ህዝቦች ልማት፣ ለእኩልነት፣ ለሰላም፣ ለዴሞክራሲ .... ባደረገው ተጋድሎ መለስ የሁሉም ብሄረሰቦች አባል የሁሉም ማህበረሰቦች የአርሶአደሩ፣ የአርብቶአደሩ፣ የወጣቱ፣ የሴቶች፣ የከተማ ነዋሪው፣ የባለሃብቱ አካል ሆኗል፡፡

## ለዴሞክራሲያዊ እሴቶችና ለህግ የበላይነት ተገዢ የሆነ መሪ!

መለስ ዴሞክራሲያዊ እሴቶችን የህይወት መመርያው ያደረገ፣ በህግ የበላይነት የሚያምን፣ ራሱን የመንግስት ባለስልጣናትንና ድርጅቱን ከህግ በታች እንጂ ከህግ በላይ አድርጐ የማይመለከት በሳል መሪ ነው፡፡ የድርጅት እንቅስቃሴ በድርጅታዊ ህገደንብ እንዲመራ የመንግስትንና የድርጅትን ሚና ግልፅ በማድረግ ጣልቃ ገብነትን ያስወገደ፣ የመንግስትና የህዝብ አስተዳደርም በህግ ማዕቀፍ ውስጥ እንዲከናወን አበክሮ የታገለና የህግ የበላይነት የሰፈነባት ሃገር ለመፍጠር ቀን ከሌት የደከመ መሪ ነው፡፡

በድርጅት ውስጥ የሚያጋጥሙ ልዩነቶች በዴሞክራሲያዊ ውይይት እና በሃሣብ ትግል መፈታት አለባቸው የሚል ፅኑ እምነት ስለነበረው ልዩነቶች አያስደነግጡትም፡፡ ያመነበትን ሃሣብ በግልፅና በህጋዊ መድረክ ላይ አቅርቦ ይከራከራል፡፡ የሚያምንበት ሃሣብ በብዙሃኑ ተቀባይነት ካላገኘ የብዙሃኑን ሃሣብ ተግባራዊ ለማድረግ ጥረት ያደርጋል፡፡ እዚህ ላይ እንደምሳሌ ሊጠቀስ የሚችለው ኤርትራ ሀገራችንን በወረረችበት ወቅት የነበረው አቋም ነው፡፡ መለስ የዓለም አቀፍ ሕግን ተከትሎ የኤርትራ መንግሥት ወራሪውን ኃይል ከግዛታችን ማስወጣት እንዳለበት ጽኑ አቋም ያዘ፡፡ በዚህም መሠረት የሃይል እርምጃ የመጨረሻው መፍትሄ መሆን አለበት እንጂ፤ ተቻኩለን ወደ ጦርነት መግባት ለአገራችን አይጠቅምም የሚል አቋም አራመደ፡፡ በዚህ ጉዳይ ላይ በተደረገው ክርክር የብዙሃኑን የኢህአዴግ አመራር ድጋፍ ባለማግኘቱ ራሱን ለብዙሃኑ ውሳኔ በማስገዛትና በሙሉ ልብ ውሳኔውን ለማስፈጸም ወደ ስራ ገባ፣ ጦርነቱንም በብቃት መራ፡፡

በተሃድሶ ዋዜማ በድርጅት ውስጥ የተከሰተውን ችግር ለመፍታት የተከተለው አቅጣጫ መለስ በአስቸጋሪ ወቅትም ቢሆን ለዴሞክራሲያዊ መርሆዎች ያለውን ታማኝነት ያረጋገጠ ነበር፡፡ የችግሮቹን መሰረታዊ ምንጭ በማጥናት እና በመተንተን በጉዳዩ ላይ ያለመታከት በመወያየትና በመከራከር እስከመጨረሻው ተንቀሳቅሷል፡፡

መለስ በአገራችን የህግ የበላይነት እንዲሰፍን፤ የፍትህ አካላት፣ የህግ አስከባሪ ተቋማት እና ሌሎች የዴሞክራሲ ተቋማት እንዲጠናከሩ እና በዴሞክራሲያዊ እሴቶች ላይ እንዲመሰረቱ ወሳኝ አመራር የሰጠ መሪ ነው፡፡ ገና ከጠዋቱ የደርግ ባለስልጣናት በህግና በህግ ብቻ እንዲዳኙ እና የበቀል እምርጃ እንዳይኖር ቁርጠኛ አቋም በመውሰድ ባለስልጣናቱ በህግ ውሳኔ እንዲያገኙ በፅኑ እምነት አመራር ሰጥቷል፡፡

የመድበለ ፓርቲ ስርአት በአገራችን እንዲጠናከር ገና ከመጀመሪያው በእምነት ሲታገል የኖረው መለስ በተለይ የ1997 ዓ.ም ምርጫ በማንኛውም መለኪያ ነፃ፣ ግልፅና ፍትሃዊ እንዲሆን ለማድረግ በምርጫ

ስነምግባር ደንብ ላይ የተመሰረተ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን በአፍሪካ ታይቶ የማይታወቅ የዴሞክራሲ ብርሃን የፈነጠቀ ተግባር እንዲከናወን ወደር የለሽ አመራር ሰጥቷል፡፡

መለስ ለህግ የበላይነት የሚታገለውን ያህል ለይቅርታም ልብ የነበረው መሪ ነው፡፡ ሰዎች ስህተታቸውን ካረሙና በህጋዊና ሰላማዊ መንገድ ከተንቀሳቀሱ በያንዳንዱ ነገር መወዛገብና 'ሰዶ ማሳደድ ውስጥ መግባት አንፈልግም' ብሎ የሚያምን ሆደ ሰፊ መሪ ነው፡፡ የተቃዋሚ ድርጅቶች አመራሮች በአገራችን ህግ መሰረት ያቀረቡት የይቅርታ ጥያቄ በአግባቡ እንዲስተናገድ አስተዋይ አመራር የሰጠ መሪ ነው፡፡ ከእስር የተፈቱ የተቃዋሚ ድርጅቶች መሪዎች በህጋዊና ሰላማዊ መንገድ ተቃውሟቸውን እንዲያራምዱ ነፃነት ያጐናፀፈ፣ ብሎም ከፓርቲዎቹ ጋር በጋራ የመስራት ፍቃደኝነትን በተግባር ያረጋገጠ ዴሞክራሲያዊ አቋም እንዲወሰድ መለስ ብልህ የሆነ አመራር ሰጥቷል፡፡ ይህ አቋሙ ማንኛውም አይነት የፖለቲካ አቋም በነፃና ሰላማዊ መንገድ መራመድ አለበት ከሚለውና በአገራችን ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ የተቃውሞ ፖለቲካና የመድብለ ፓርቲ ስርአት እውን እንዲሆን በድፍረት ካራመደው በሳል አቋም ጋር የሚያያዝ ነው፡፡

መለስ ለአለም አቀፍ ህግና ስርአትም ራሱን ያስገዛ መሪ ነው፡፡ የኢትዮ-ኤርትራ ጦርነት ጉዳይ በተመለከተ በዓለምአቀፍ የዳኝነት መድረክ የተወሰኑ ውሳኔዎች አንዳንዶቹ ችግር ያለባቸው ቢሆኑም ውሳኔውን በመቀበል ተግባራዊነቱ ዘላቂ ሰላምና ጉርብትናን በሚፈጥር መልኩ በድርድር እና በሰጥቶ መቀበል መርህ ማዕቀፍ እንዲታይ አቋም በመውሰድ ለህግ የበላይነት ብቻ ሳይሆን ለዘላቂ ሰላም የአመራር ብቃቱን አሳይቷል፡፡

## ዕውቀትን ለማካበት ሁሌ የሚተጋ ሁለገብነትን የተጐናፀፈ በሳል መሪ!

መለስ ገና በጎልማሳነቱም ወቅት እውቀትን ለማካበት በእጅጉ ይጥር ነበር፡፡ ድህነትን መግደል የሚቻለው በእውቀት ጥይት ነው የሚል መርህን የሚከተለው መለስ ቀን ከሌት በማንበብና ከሰዎች ጋር በመወያየት ዕውቀቱን የማዳበር ልዩ ተሰጥኦ ነበረው፡፡

መለስ ዕውቀቱን የሚያዳብረው የያዘውን ዓላማ ከግብ ለማድረስ የሚያስችለውን ዓቅም ለመፍጠር ነው፡፡ የትግሉን መስመሮች ለመንደፍ የተለያዩ አገሮችን ልምድ አጥንቷል፣ የተለያዩ የኢኮኖሚ ዘርፎችን መርምሯል፣ የወታደራዊ ሳይንስ መድበሎችን አገላብጧል፡፡ ከዚህ የካበተ የዕውቀት ባህር ለትግሉና ለአገሩ የሚጠቅሙ ልምዶችን የመቀመር፣ ከአገራችን ሁኔታ ጋር አስተሳስሮ የመተንተንና የመጠቀም አቅም አዳብሯል፡፡

ስለጐረቤቶቻችንና ስለአፍሪካ ሰፊና ጥልቅ ዕውቀት ያለው በመሆኑ የአካባቢው መሪዎችና ታዋቂ ሊቃውንት ዘወትር የርሱን አስተያየትና ምክር ይጠይቃሉ፡፡ የሚሰጣቸው አስተያየት በጥልቅ ዕውቀት ላይ የተመሰረተና ነባራዊ በመሆኑ አድናቆታቸውን ይገልፃሉ፡፡ መለስ ለኢትዮጵያ፣ ለአፍሪካና ለዓለም ህዝቦች የሚበጅ መስሎ ከተሰማው የትኛውንም የዕውቀት ዘርፍ ለመካን ፍላጐቱም ሆነ ችሎታው ወደር የለውም፡፡

በመሆኑም መለስ በአንድ ጊዜ የፖለቲካ ሳይንቲስት፣ የኢኮኖሚ ሊቅ፣ የማህበራዊ ሳይንስ ተንታኝ፣ የህግ ምሁርና የወታደራዊ ሳይንስና ጥበብ ቁንጮ ነበር ማለት ይቻላል፡፡

በአሁኑ ወቅት አገራችን የምትመራባቸው የተለያዩ የፖሊሲና ስትራቴጂ አቅጣጫዎች በተለይም የውጪ ጉዳይ ደህንነት ፖሊሲ እንዲሁም ቅድሚያ ለሰላም የሚሰጠው የሰራዊት ግንባታ አቅጣጫ የመለስ የሰላ አእምሮ ያመነጫቸው ናቸው፡፡

መለስ  ኒዮሊበራሊዝም በተባለውና ለበርካታ ዓመታት በምዕራብ የበለፀጉ አገሮችና በዓለማቀፍ መሪ ኢኮኖሚያዊ ድርጅቶች ዘንድ ገዢነት ያገኘውን አስተሳሰብ መሰረታዊ ጉድለቶች በማያወላዳ መንገድ ግልፅ አድርጓል፡፡ ይህ አስተሳሰብ በተለይ እኛንና እኛን በመሰሉ አገሮች ላይ የሚያስከትለውን ችግር በዝርዝር ተንትኗል፡፡ በዚህ ብቻ ግን አላበቃም ለታዳጊ አገሮች ከዚህ አስተሳሰብና ስርአት የተለየ አማራጭና አዋጪ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ስርአት አመላክቷል፡፡ ይህና መሰል የመለስ ምርምሮች በአገራችን ያስከተሉትን የአስተሳሰብ፣ የዕቅድ፣ የተግባርና የተስፋ ሰፊና ጥልቅ ለውጥ መገንዘብ ይገባል፡፡

ቀድሞ ባንድ በኩል ያገራችን ነባር አስከፊ የኑሮ ሁኔታ፣ በሌላ በኩል በተለምዶ ተቀባይነት የነበረው የኢኮኖሚ ዕውቀት ተጣምረው በአገር ውስጥም ሆነ በውጭ ስለዕድገት የነበረው አመለካከት ከድህነት ወደ ብልፅግና የሚወስደው ጉዞ የግድ ደረጃ በደረጃና በመጠኑ እየተሻሻልን ከዓመታት በኋላ ቀስ በቀስ የብልፅግና ብልጭታ ማየት እንጀምራለን የሚል ነበር፡፡ መለስ ይህንን ዘገምተኛና ውስን ሂደት አሻፈረኝ በማለት በድፍረት ከወዲሁ ለከፍተኛና ፈጣን ሁሉንም የሕዝብ ወገን --- ገበሬውን፣ አርብቶ አደሩን፣ ሴቱን፣ ወጣቱን፣ ከተሜውንና ነጋዴውን --- አሳትፎና ጠቅሞ ድህነትን ቶሎ ወደሚያወድም አቅጣጫ መራን፡፡ በግልፅ በሁሉም ዘንድ እንደሚታየው፣ መለስ የከፈተው አዲስ የልማት አካሄድ ገና ከጅምሩ በየአቅጣጫው አጥጋቢ ውጤት ከማስመስከሩም በላይ፣ አይከጀልም ሲባል የኖረው እንደሚቻል ስላረጋገጠልን በራሳችን ብቃት ጠንካራ እምነት፣ በወደፊት ዕድላችን ሙሉ ተስፋ አሳደረብን፡፡

መለስ ማንኛውም አስተሳሰብ መመዘን ያለበት ለሰፊው ህዝብ ከሚያስገኘው ፋይዳ አኳያ ነው የሚል ፅኑ እምነት አለው፡፡ ከግራ ዘመም የፖለቲካ ታሪክ የትግል እርምጃውን የጀመረው መለስ ያ አቅጣጫ ከህዝቡ ጥቅም አኳያ ሚዛን የማይደፋ ሆኖ ሲያገኘው እርሱን አሽቀንጥሮ ለህዝቡ የሚጠቅመውን ለማንሳት አይኑን ያላሸ፣ ከሁኔታዎች ጋር የሚራመድ፣ ነገር ግን ዋነኛ ዓላማውንና መርሁን የማይለቅ መሪ ነው፡፡ በርካታ የውጪ መሪዎች መለስ በመሰረታዊ አገራዊ ጥቅም ላይ የማይደራደር መሆኑን በአድናቆት ይገልፃሉ፡፡

ይህ ሰፊ የዕውቀት አድማስ አዲስና ስርነቀል የፖለቲካ ኢኮኖሚ ለውጥ የሚያመጡ ፖሊሲዎች ለማፍለቅ፣ እጅግ የገዘፈ ራዕይና ለማመን የሚያስቸግሩ የተለጠጡ ግቦችን ያለሙ ዕቅዶችን ለማውጣት ረድቶታል፡፡ የመለስ የዕውቀት ልህቀት አዳዲስ አስተሳሰቦችንና በምክንያታዊ ዘይቤዎች የተቃኙ መሰረታዊ መርሆዎችን መንደርደሪያ ያደረጉ የችግር አፈታት ጥበቦችን ያስተሳሰሩ በመሆናቸው ሁልጊዜም ውጤታማ ነበሩ፡፡

### *መላ ህይወቱን ላመነበትና ለቆመለት ዓላማ መስዋዕት ያደረገ መሪ!*

*መለስ ከአንድ ትውልድ በላይ ለሆነ ዓላማ እስከ ዕለተ ሞቱ በታታሪነት ሲታገል የኖረ፣ ስለ ግል ጥቅሙና ምቾቱ የማያስብ፣ የግል ዝናና ክብር የማያማልለው ታጋይና ህዝባዊ መሪ ነው፡፡ ዘወትር ከአንደበቱ 'ከድህነት በላይ ጠላት የለንም' የሚለው አባባል አይጠፋም፡፡ ትኩረቱ ሁሉ ከወጣትነቱ ጀምሮ በልቡ ውስጥ የሰረፀውን የህዝቦችን ሰቆቃ የማስቀረት ራዕይ ማሳካት ላይ ነው፡፡ በልጅነት ልቡ የህክምና ትምህርትን ለመከታተል የወሰነው የአካባቢው ነዋሪዎች በህክምና እጦት ይደርስባቸው የነበረውን ችግር በማጤን ነው፡፡ በትጥቅ ትግሉ ወቅት የተደረገውን ተጋድሎ ድህነትን ለማጥፋት በሚደረገው ትግል ጐዳና ላይ ያለውን 'የድህነትን ዘበኛ' ለማስወገድ የተደረገ ጥረት አድርጐ የሚቆጥረው መለስ ዋነኛው ትግል አሁን ድህነትን ለማሸነፍ የምናደርገው ትግል ነው በማለት አጥብቆ አስተምሯል፡፡*

*አገራችን ከድህነት ውርደት መውጣት አለባት በማለት በቁጭት የሚናገረው መለስ ድህነት በሰብአዊነት ላይ የሚያሳርፈውን ጥቁር ጥላ ህዝቦች እንዲገነዘቡ አበክሮ ይሰራል፡፡ ይህ ፀረ-ድህነት ትግሉ ለህዝቡ ካለው ጥልቅ ፍቅር የሚቀዳ ነው፡፡ በ1977 ዓ.ም የትግራይ ህዝብ በረሃብ በሚረግፍበት ወቅት ወጣቱ ታጋይ መለስ ዜናዊ 'የምታገልለት ህዝብ በረሃብ የሚረግፍ ከሆነ የኔ መታገል ትርጉም የለውም፡፡ እነዚህ ህዝቦች በረሃብ የሚረግፉት የዘመናዊ ግብርና እውቀት ስለሌላቸው ነው' በማለት የችግሩን ጥልቀትና የመፍትሄ አቅጣጫውን አጣምሮ ይገልጻል፡፡*

*በኤርትራ ጦርነት ወቅት ዋነኛ ጠላታችን ድህነት ነው፡፡ ተጣድፈን ወደ ጦርነት መግባት በድህነት ላይ የምናካሂደውን ጦርነት ከማደናቀፉም በላይ ያለንን ቁሳዊና ሰብአዊ ሃብት በማሚጠጥ ልንወጣው የማንችለው ቀውስ ውስጥ ይከተናል በማለት በአስቸጋሪ ወቅትም ቢሆን ከፀረ ድህነት ትግሉ ላይ ትኩረቱን ለማንሳት እንደማይሻ ያስመሰከረ የፀረ-ድህነት ትግል አርበኛ ነው፡፡*

*ይህ የፀና እምነቱ አገራችን ከድህነት አረንቋ ወጥታ በፈጣን የዕድገት ጐዳና ላይ እንድትገሰግስ፣ በመሆኑም የሰላም፣ የዴሞክራሲና የሰብአዊነት መሰረት እንዲጠናከር ብቁ የሆነ አመራር ለመስጠት አስችሎታል፡፡*

### *ባለራዕይ አፍሪካዊ መሪ!*

*የመለስ የአመራር ሚና እንደ አንድ የድርጅት መሪ እና እንደ አንድ አገር መሪ ብቻ የሚወሰን አይደለም፡፡ መለስ አህጉራዊና ዓለምአቀፋዊ የመሪነት ሚና መጫወት የጀመረ በአፍሪካ አህጉርም ሆነ በዓለምአቀፍ ደረጃ አክብሮትና አድናቆት የተሰጠው ድንቅ መሪ ነው፡፡*

*መለስ አጠቃላይ ዓለማቀፍ የፖለቲካና የኢኮኖሚ ሁኔታዎችን በማጥናትና በመተንተን ብቃት የተካነ መሪ ነው፡፡ በተለያዩ መድረኮች ያሉትን ለውጦች የማጤን፣ ለውጦቹ በትግሉና በአገራችን ላይ የሚኖራቸውን ተፅእኖ የመተንተን፣ በዚያ ላይ ተመስርቶም ለትግሉና ለአገራችን የሚበጁ አቅጣጫዎችን የመቀየስ አቅም አለው፡፡ በትምህርትና ምርምር ባካበተው እውቀት የአለምን የሃይል ሚዛንና አሰላለፍ፣ የአፍሪካን ጂኦፖለቲካዊ ክብደት፣ የአለምን የኢኮኖሚ መስተጋብር፣ የዓለምአቀፍ ተግዳሮቶችን ባሕርይና*

እነዚህ ሁሉ በአፍሪካም ሆነ በአገራችን ላይ የሚያሳድሩትን ተፅእኖ ይመረምራል፡፡ ከዚህ የሚገኙ ውጤቶችን መሰረት በማድረግም አዎንታዊ አዝማሚያዎችን ለማጠናከርና ለመጠቀም አሉታዊ አዝማሚያዎችን ደግሞ ተፅእኗቸውን ለመቀነስና ለመመከት የሚያስችሉ የፖሊሲ አቅጣጫዎችን ያመነጫል፡፡

መለስ ከቅርብ አመታት ወዲህ የአፍሪካ ድንቅ ልጅ የሚል ስያሜ ያተረፉለትን የተለያዩ ተግባራት አከናውኗል፡፡ የአፍሪካ ምርቶች ዋጋ እንዲሻሻል፤ ወደ አፍሪካ የሚፈሰው ኢንቨስትመንት፣ ብድርና እርዳታ እንዲጨምር፤ አፍሪካውያን በአየር ንብረት መዛባት ለሚደርስባቸው ጉዳት ማካካሻ እንዲያገኙ እንዲሁም የአለም የንግድ ስርአት ለአፍሪካ ዕድገት የሚያመች እንዲሆን ለማድረግ በተገኙት መድረኮች ሁሉ ታግሏል፡
፡

የአፍሪካውያን ጥቅም የሚረጋገጠው በተናጠል በሚደረግ መፍጨርጨር ሳይሆን በመሰረታዊ የጋራ ጥቅም ጉዳይ ላይ የጋራ አቋም በመያዝ፣ በዓለምአቀፍ መድረኮች በአንድ ድምፅ በመሰለፍ መሆኑን መለስ ከልቡ ያምናል፡፡ ለዚህም ተግባራዊነት ከአፍሪካውያን መሪዎች ጋር በመመካከርና ጠቃሚ ሃሣቦችን በማቅረብ ተቀባይነትንና አክብሮትን አትርፏል፡፡

መለስ የአካባቢው ሀገሮች ያለን እድል ተሳስረንና ተባብረን መልማትና ማደግ ነው የሚል ጽኑ እምነት አለው፡፡ አገራችንንና የአካባቢውን አገሮች በመሰረተ ልማት ለማስተሳሰር ቆራጥ እርምጃዎችን ወስዷል፡፡ በአባይ ወንዝ ፍትሃዊ ተጠቃሚነት ላይ ያራመደው አቋም ለዘመናት በአካባቢው ሰፍኖ የቆየውን ኢ-ፍትሃዊ አስተሳሰብ የሸረሸረና የጋራ ተጠቃሚነት መንፈስ በተፋሰሱ አገሮች ዙሪያ ተቀባይነት እንዲያገኝ ውጤታማ ስራ የሰራ ጠንካራ መሪ ነው፡፡ መለስ ከሁሉም ጐረቤቶቻችን ጋር በሰላም፣ በጋራ ጥቅምና በእኩልነት ላይ የተመሰረተ ግንኙነት ማድረግ ዞሮ ዞሮ ጠቀሜታው ለኛ ነው የሚል የፀና አቋም አለው፡፡

በድርድርና በውይይት ሊፈታ ያልቻለ እንዲሁም በህዳሴ ጉዟችን ላይ የተጋረጠ እንቅፋት ካልሆነ በቀር በምንም አይነት መልኩ ከጐረቤቶቻችን ጋር ወደ ግጭት መግባት የለብንም፤ ሲሆን ሲሆን 'ከመንገዳችን ወጥተንም' ቢሆን ለጐረቤቶቻችን ሉዓላዊነትና ብሄራዊ ጥቅም መስራት አለብን የሚል ቁርጠኛ አቋም በተገኘው አጋጣሚ ሁሉ አራምዷል፡፡

እነዚህ የመለስ አፍሪካዊ አቋሞች በተቋም ደረጃ እንዲፈፀሙ በራሱ ሃሣብ አመንጪነትና ግንባር ቀደም ተሳትፎ ተመስርቶ ውጤታማ ተግባር ያከናወነው የኔፓድና የኢጋድ ተቋማት ለዚህ ምስክር ናቸው፡፡ መለስ በአፍሪካ ህብረት ደረጃም አገራችን የፅ/ቤቱ መቀመጫ እንድትሆን ብቻ ሳይሆን የአፍሪካን ጥቅም ለማራመድ የሚያስችሉ አቋሞችን የሚወስድ ተቋም እንዲሆን ያለ መታከት ሰርቷል፡፡ በተለይም ከአየር ንብረት ለውጥ ጋር በተያያዘ የአፍሪካን ድምፅ በማስተጋባት የአፍሪካ ቃል አቀባይ (Spokesman of Africa) የሚል ስያሜ ያገኘ ድንቅ የአፍሪካ ልጅ ነው፡፡

በተደጋጋሚ በG-8 እና በG-20 ስብሰባ ላይ አፍሪካን ወክሎ እንዲገኝ የሚጋበዘው መለስ በኮፐንሃገን፣ ደርባንና ዳቮስ ላይ በተካሄዱት የመሪዎች ስብሰባ ላይ የአፍሪካን ጥቅሞች በመወከል ያደረገው ክርክር አንቱታን አትርፎለታል፡፡ ይህ አካሄድ ለዘመናት አፍሪካ በእንደዚህ አይነት መድረኮች የነበራትን

የተሰፈኝነት ሚና የቀየረና አፍሪካን ወደ ተደራዳሪነት ያሸጋገረ በመሆኑ ለአፍሪካ አዲስ ምዕራፍን የከፈተ ነበር፡፡

መለስ በአፍሪካውያን ዘንድ በአድናቆት ከሚነሳባቸው ጉዳዮች አንዱ ለአፍሪካ ሰላም ያደረገው አስተዋፅኦ ነው፡፡ በአፍሪካ ውስጥ የተከሰቱ ግጭቶችን ለመፍታትና መግባባትን ለመፍጠር የተጫወተው የአደራዳሪነትና የግጭት አፈታት የመሪነት ሚና በእጅጉ የሚደነቅ ነው፡፡ መለስ በአፍሪካ ደረጃ በሶማሊያ፣ በሱዳን፣ በሩዋንዳ፣ በቡሩንዲና በላይቤሪያ ሰላም እንዲሰፍን አገራችን የድርሻዋን እንድትወጣ በአፍሪካውያን ወንድሞቻችን ዘንድ የሚወደስ ሰላም የመፍጠርና የሰላም ማስከበር ተልእኮዎችን በፍፁም አፍሪካዊ መንፈስ ሲመራ የኖረ ታላቅ አፍሪካዊ መሪ ነው፡፡

መለስ በዓለምአቀፍ መድረኮች ከሌሎች የአለም መሪዎች ጋር የሚያደርጋቸው ውይይቶች ከፍተኛ አክብሮትን አትርፈውለታል፡፡ እጅግ በሳልና አንደበተ ርቱዕ ነው በማለት የሚገልፁት ታላላቅ የአለም መሪዎች መለስ የአገራችንን ልማት ለማፋጠን፣ ለአካባቢያችን ሰላምና መረጋጋት፣ ለሚያደርገውን እንቅስቃሴና ለፀረ-ሽብርተኝነት አቋሙ አድናቆታቸውን ይገልፃሉ፡፡ በግል ባህሪው፣ በታታሪነቱና በአቋም ፅናቱም ያወድሱታል፡፡ በአመራር ብቃቱ የአገራችንን ብቻ ሳይሆን የአፍሪካን ህዳሴ እውን ለማድረግ የሚታገል የአፍሪካ ታላቅ መሪ መሆኑንም አበክረው ይገልፃሉ፡፡

## መለስን መለስ እንዲሆን ያደረገው ምንድነው?

መለስ ለብዙዎች በእጅጉ የሚያስደንቅ ጠንካራ ሰብእና እንዲኖረው፣ በወጣትነቱ የመሪነት ክህሎት እንዲላበስ እና ዘርፈ ብዙ ጥንካሬዎችን እንዲያካብት ያደረገው ምንድ ነው ብለው የሚጠይቁ በርካቶች ይኖራሉ፡፡ መለስን መለስ ያደረጉ ገና ከልጅነቱ ጀምሮ ማንነቱን ሲቀርፁ የኖሩ በርካታ ከባቢያዊ ምክንያቶች የመኖራቸውን ያህል የተለዩ የግል ባህሪያትም አሉት፡፡ ሁሉንም ምክንያቶች መዘርዘር ቢያዳግትም ጎላ ያሉትን መጥቀስ ግን ይቻላል፡፡

እንደማንኛውም ታጋይ ሁሉ መለስ የድርጅቱ የህወሓት/ኢህአዴግ ውልድ ነው፡፡ መለስ መለስ ሊሆን የቻለው በውይይት በሚያምን፣ በተመሳሳይ አቋም የተሰለፉ አባላትን ባቀፈ፣ ህዝቡንም በዴሞክራሲያዊ መንገድ ባሰለፈ ዴሞክራሲያዊና ህዝባዊ ድርጅት ውስጥ በመታቀፉ ነው፡፡ መለስም በተደጋጋሚ እኔን የፈጠረኝ ኢህአዴግ ነው በማለት የርሱ መሰረታዊ እሴቶች ከኢህአዴግ መሰረታዊ እሴቶች የተቀዱ መሆናቸውን ይገልፅ ነበር፡፡ መለስ የድርጅቱን ዓላማዎች የህይወቱ መመሪያ አደረጋቸው፡፡ ኢህአዴግን ከመሰለ ድርጅት ውጪ መለስን የመሰለ ሰው ይፈጠራል ብሎ ማሰብ የሚቻል አይሆንም፡፡ ይህን ከድርጅቱ የወረሰውን ስብእና አጐልብቶና አጠናክሮ በመግለፅ እንዲሁም የራሱን የግል ስብዕና ለድርጅታዊ ተልእኮው በማስገዛት መለስን መለስ ሊያደርገው የቻለው ሁኔታ ተፈጠረ፡፡

መለስ የላቀ ህዝባዊ ፍቅር ያለው መሪ ነው፡፡ ይህ ጥልቅ ህዝባዊ ፍቅር መለስ እያንዳንዷን ጉዳይ ከህዝቦች ጥቅም አኳያ እንዲመዝን አድርጐታል፡፡ የህዝቦች ሰቆቃ የሚያንገፈግፈው፣ ለህዝቦች ጥቅምና ደህንነት ቀን ከሌት የሚጨነቅ ይህንን ፍቅሩን የሁሉም ተግባራቱ አንቀሳቃሽ ሞተር አድርጎ የሚጠቀም

መሆኑ መለስን መለስ አድርጎታል፡፡ የህዝቦችን ፍላጎት የሚያነፈንፍ ለህዝብ የቀረበ ልብ አለው፡፡ ለኔ አገር ማለት ህዝብ ማለት ነው፡፡የአገር ፍቅርም ማለት ከህዝብ ፍቅር ውጪ ትርጉም የለውም ይላል መለስ፡፡ ህዝብ በትክክለኛ ድርጅት ከተመራ ታሪክ ሊሰራ የሚችል መሆኑን አምኖ ወደ ጥቅሙ የሚያመራውን አቅጣጫ ለማስያዝ መለስ ሁልጊዜ ይጥራል፡፡

መለስ ለብዙሃኑ የኢትዮጵያ ህዝቦች-ለአገራችን አርሶአደሮች እና አርብቶ-አደሮች -ወገንተኝነቱ የጐላ ነው፡፡ የአገራችንን መፃኢ ዕድል የሚወስነው በአርሶ አደሩ ህይወት ላይ የምናመጣው ለውጥ ነው ብሎ ያምናል፤ አጠንክሮም ይሰራል፡፡

መለስ ለሴቶችና ለወጣቶች ያለው ወገንተኝነትም ከፍተኛ ነው፡፡ ወጣቱን እውቀት እናልብሰው፣ ድህነትን የማጥፊያ አቅጣጫ እንጠቁመው፣ መጪዋን ኢትዮጵያ የሚረከብበት ጉልበት እንዲያገኝ እንገንባው ይላል፡፡ የህዝቦች የነፃነት ደረጃና የሃገራትም የዕድገት ልክ የሚመዘነው በሴቶች የነፃነትና የተጠቃሚነት መጠን ነው የሚል ዕምነት አለው፡፡ ሁልጊዜ ሴቶች ተጠቃሚ የሚሆኑበትን አቅጣጫ ይማትራል፡፡ በአገራችን ታሪክ ታይቶ በማይታወቅና  ድንበር፣ ዘር፣ ፆታ፣ እምነት ባልገደበው ሁኔታ የመላ አገሪቱን ህዝቦች ፍቅር የተጐናፀፈው በዚህ ምክንያት ነው፡፡

መለስ የማይናወጥ የዓላማ ፅናት ያለው መሪ ነው፡፡ መለስ ላመነበት ዓላማ በቁርጠኝነት እስከመጨረሻው የሚታገል መሪ ነው፡፡ ያሰበውንና ያለመውን ጉዳይ ለማሳካት የሚያስችል የታመቀ ውስጣዊ ሃይል አለው፡፡ እያንዳንዷን ጉዳይ ከተነሳበት ዓላማና ከጨበጣቸው መርሆዎች አኳያ ይመዝናል፡፡ ከሰዎች ባህሪ አምርሮ የሚጠላው መርህ አልባነትን ነው፡፡

መለስ በቀጣይነት የሚማር የተማረውንም ለተነሳበት ዓላማ የሚያውል መሆኑ ሌላው የርሱ መገለጫ ነው፡፡ መለስ ያነባል፣ ይጠይቃል፣ ያዳምጣል፣ ያጠናል፣ ያወቀውን ያሳውቃል፣ ዕውቀቱን ተግባር ላይ ያውላል፤ ከተግባሩም ይማራል፡፡ ይህ የማያቋርጥ የመለስ የእንቅስቃሴ ምህዋር ነው፡፡

መለስ በእንቅስቃሴ ውስጥ የሚኖር ነው፡፡ ሁልጊዜም በተግባራዊ እንቅስቃሴ ወስጥ ተጠምዶ ይኖራል፡፡ ከተግባራት ውስጥ ቁልፉን ጉዳይ ለይቶ እዚያ ላይ ይረባረባል፡፡ ከማነቆዎችም ዋነኞቹን ለይቶ እነርሱን ለመፍታት ሙሉ አቅሙን ይጠቀማል፡፡ መለስ ማንም ከሚገምተው በላይ በሁሉም ጉዳዮች ላይ በቂ መረጃ አለው፡፡ እንዳንዴም መረጃው ሊኖራቸው ይችላል ተብሎ ከሚገመቱት ሰዎች በላይ መረጃ ኖሮት ይገኛል፡፡ በእንቅስቃሴ ውስጥ ሁሉም ነገር መፍትሄ ይኖረዋል ብሎ ያምናል፡፡

ዋነኛውና ትልቁ የመለስን ባህሪ የቀረፀው በድህነት ላይ ያለው የመረረ ጥላቻ ነው፡፡ የሁሉም ነገር ማጠንጠኛው ፀረ ድህነት ትግሉ ነው፡፡ የአገራችን ህዝቦችም ሆኑ መላው የአፍሪካ ህዝቦች ድህነት አይገባቸውም በማለት ከድህነት መውጫ ቀዳዳ ሲያማትር ዕድሜውን ሙሉ አሳልፏል፡፡ መለስ ድህነት ባለበት ሁኔታ የአገር ሰላም ሊረጋገጥ አይቻልም፣ ዴሞክራሲም ሊሰፍን አይችልም፣ እንዲያውም ድህነት የዜጎችን ሰብአዊነት እና ክብር የሚደፍቅ ነቀርሳ ነው የሚል የፀና እምነት ነበረው፡፡ መላ ህይወቱን በትግል ሲንጠው የነበረው ይኸው ፀረ-ድህነት ጠንካራ አቋሙ ነው፡፡

መለስ ይህንን ፀረ ድህነት አላማውን ከግብ ለማድረስ የሚያስችሉ የፖሊሲ ማዕቀፎችን ለአገራችን ብሎም ለመሰል ህዝቦች በሚሆን መልኩ ቀምሯል፡፡ በድህነት ላይ የጀመረው ሁሉን አቀፍ ዘመቻ ተጠናክሮ በአገራችን ሰፊና ፈጣን የልማትና የዕድገት ጉዞ ተጀምሯል፡፡ መለስ አገራችን ከድህነት ለመውጣት ትክክለኛ አቅጣጫ ይዛ መራመድ ስትጀምር ያንን ግዙፍ ራዕዩን ለትውልድ አስጨብጦ አለፈ፡፡ የአገራችን ህዝቦች በተለይም ወጣቶችና ሴቶች የመለስ ዕረፍት ከተሰማ ጀምሮ ራዕዩን አንግበን እንቀጥላለን በማለት የገቡት ቃልኪዳን መለስን ከመቃብር በላይ ለዘመናት ሊያኖር የሚችል ትውልድ መፈጠሩን አብስሯል፡፡

ዛሬ መለስ በዐፀደ ሥጋ በመካከላችን ባይኖርም፣ በሓሳቡ፣ በግብሩ፣ ከሁሉም በላይ በጥረቱና በራዕዩ ሩቅነት በመንፈሳችን ይኖራል፡፡ ስለዚህም “አለ” ፤ “ነው” እያልን ተናገርን፡፡ ትቶት ያለፈው ገፁ ብዙ አብነቱ አብሮን እንዳለ ወደፊትም ሲታወስ ይኖራል፡፡

ወደፊትም የታሪክ ተማሪዎች የትም ለተበደለው ወገን በአዲስና ጽኑ መንፈስ ከቆሙላቸው ጥቂት የዘመናችን ታላላቅ የዓለም መሪዎች መካከል እንደሚያጤኑት እምነታችን ነው፡፡

ባለቤቱ አዜብና ልጆቹ ሰምሀል፣ ማርዳ፣ ሰናይና በረከት ጽናትና ብርታት እንዲያገኙ ከልብ እንመኛለን.. እንዲሁም ቤተዘመዱ፣ ጓዶቹና ወዳጆቹ ጽናት ያግኙልን እስከመጨረሻው ሰዓት እረፍት ነስተንሃልና መለስ በሰላም እረፍ፡፡